4350.3 REV-1

“ይህ ሰነድ በHUD የተዘጋጀው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህ ሰነድ ተተርጉሞ እንዲደርስዎ የተደረገው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ሲባል ብቻ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የዚህ ሰነድ ቅጂ ነው፤ ኦፊሴላዊነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈጻሚነት የሚኖረው። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።”

---

# ኤግዚቢት 7-4፦ **ናሙና** የዓመታዊው የድጋሚ ማረጋገጫ ሦስተኛ ማሳሰቢያ/የውል መቋረጥ ማሳሰቢያ

(የተከራይ ስም / Tenant’s Name)
(አድራሻ / Address)

(ቀን፣ ከመጪው የድጋሚ ማረጋገጫ ቀን ቢያንስ 60 ቀን በፊት / Date, at least 60 days prior to the upcoming recertification anniversary date)

ውድ _________፦

የድጋሚ ማረጋገጫ ቃለ መጠይቅ ቀጠሮ እንዲይዙ የሚጠይቅ ማስታወቂያ በ(የመጀመሪያው ማሳሰቢያ ቀን / Date of First Reminder Notice) እና በ(ሁለተኛው ማሳሰቢያ ቀን / Date of Second Reminder Notice) ልከንልዎታል። እስካሁን ድረስ ለቃለ መጠይቁ ቀጠሮ አልያዙም። በኪራይ ውልዎ አንቀጽ [15፣ 10 ወይም 9—ለተከራዩ በተሰጠው ሞዴል የኪራይ ውል ላይ ያለውን ተገቢውን አንቀጽ ቁጥር ያመልክቱ / 15, 10 or 9–indicate the paragraph number that corresponds to the paragraph of the model lease being used for the tenant] ላይ እንደተጠቀሰው የቤቶች አስተዳደርና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (Department of Housing and Urban Development (HUD)) በየዓመቱ ገቢዎንና የቤተሰብዎን አወቃቀር በመገምገም የኪራዩንና የሚያገኙትን እገዛ መጠን እንደገና እንድንገመግም ያስገድደናል።

ገቢዎንና የቤተሰብዎን አወቃቀር የመገምገም ሥራችንን ማጠናቀቅ እንችል ዘንድ የግድ ከ(የተከራዮች ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ፣ ከኪራይ ጉዳይ ጸሐፊ፣ ወዘተ. / Resident Manager, Occupancy Clerk, etc.) ጋር በ(የቃለ መጠይቁ ቦታ / place of interview) መገናኘት እና አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች መስጠት **እንዲሁም ፊርማዎች መስጠት ይጠበቅብዎታል። በፕሮግራሙ ውስጥ ያለዎት ተሳትፎ እንዲቀጥል ድጋሚ ማረጋገጫ ለመስጠት ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር ተስማምተው መገኘት ይኖርብዎታል።** (የተከራዮች ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ፣ የኪራይ ጉዳይ ጸሐፊ፣ ወዘተ. / Resident Manager, Occupancy Clerk, etc.) የድጋሚ ማረጋገጫውን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ (የሚገኙበት ቀንና ሰዓት / dates and times available) ይገኛሉ። ለቃለ መጠይቁ ቀጠሮ ለማስያዝ እባክዎን በተቻለ ፍጥነት (የተከራዮች ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ፣ የኪራይ ጉዳይ ጸሐፊ፣ ወዘተ. / Resident Manager, Occupancy Clerk, etc.)ን (በስልክ ወይም በጽሕፈት ቤት / by phone, at the office) ያነጋግሩ።

ከ(የተከራዮች ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ፣ የኪራይ ጉዳይ ጸሐፊ፣ ወዘተ. / Resident Manager, Occupancy Clerk, etc.) ጋር ተገናኝተው አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ከሰጡ **እንዲሁም ፊርማዎን ካኖሩ** ገቢዎ እገዛውን ለማግኘት ብቁ እንዳልሆኑ የሚያረጋግጥ ካልሆነ በቀር የሚያገኙትን እገዛ አናቋርጥብዎትም። የኪራይ ጉዳይ ቢሮውን ያነጋገሩት ከ(ከመጨረሻው ዓመታዊ የድጋሚ ማረጋገጫ በኋላ ያለውን 11ኛ ወር 10ኛ ቀን ያስገቡ / insert the cutoff date, the 10th day of the 11th month after the last annual recertification) በኋላ ከሆነ የድጋሚ ማረጋገጫውን ሂደት እናከናውንልዎታለን፤ ሆኖም ማንኛውንም የኪራይ ጭማሪ በተመለከተ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ አይሰጥዎትም።

**የድጋሚ ማረጋገጫውን ሂደት ለማከናወን ይረዳን ዘንድ ለቃለ መጠይቅ ሲመጡ የሚከተሉትን መረጃዎች ይዘው መገኘት ይኖርብዎታል፦
(አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በሙሉ ይዘርዝሩ። / List all required information)**

(**ማስታወሻ፦**<u>ከPRAC ፕሮጀክቶች በስተቀር</u> ለሁሉም ፕሮጀክቶች ተከራዮች የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር ይጨምሩ። / **NOTE:** For tenants of all projects, <u>except PRAC projects</u>, add the following.) ከ(የድጋሚ ማረጋገጫው ዓመት የሚሞላበትን ቀን ይጻፉ / insert recertification anniversary date) በፊት ምላሽ ሳይሰጡ ከቀሩ በኪራይ ውልዎ አንቀጽ [15 ** ወይም ** 14 / paragraph 15 ** or ** 14] የሚያገኙትን እገዛ የማቋረጥና (** የኪራዩን ዓይነት፣ ካልሆነም** የገበያውን ኪራይ፣ የውል ኪራይ ወይም **የ BMIR 110% ኪራይ ያስገቡ / **insert type of rent, either** market rent, contract rent or **110% of BMIR rent) $______(ተከራዩ እንዲከፍል የሚጠበቅበትን ኪራይ መጠን ይጥቀሱ / insert the rent the tenant will be required to pay)** ከ(የድጋሚ ማረጋገጫው ዓመት የሚሞላበትን ቀን ይጻፉ / insert the recertification anniversary date) አንስቶ እንዲከፍሉ የመጠየቅ መብት ይሰጠናል። **ይህ የኪራይ ጭማሪ የሚደረገው ተጨማሪ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥዎ ይሆናል። ጭማሪ የተደረገበትን ኪራይ ሳይከፍሉ ከቀሩ የኪራይ ውልዎን ልናቋርጠውና ውሉን የማቋረጡን ውሳኔ በፍርድ ቤት ተፈጻሚ እንዲሆን ልናስደርግ እንችላለን።**

"ይህ ሰነድ በHUD የተዘጋጀው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህ ሰነድ ተተርጉሞ እንዲደርስዎ የተደረገው መብቶችዎንና ግዴታዎችዎን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ሲባል ብቻ ነው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የዚህ ሰነድ ቅጂ ነው፤ ኦፊሴላዊነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈጻሚነት የሚኖረው። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።"

(**ማስታወሻ፡** በPRAC ፕሮጀክቶች ውስጥ ላሉ ተከራዮች የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር ይጨምሩ። / **NOTE**: For tenants in PRAC projects add the following sentence.) ከ(የድጋሚ ማረጋገጫው ዓመት የሚሞላበትን ቀን ይጻፉ / insert the recertification anniversary date) በፊት ምላሽ ሳይሰጡ ከቀሩ የኪራይ ውልዎ ሊሰረዝ ይችላል።

እባክዎን ኪራይ እንድንጨምርብዎ አያድርጉን። ዛሬውኑ የኪራይ ቢሮ (Rental Office) ሄደው ለቃለ መጠይቁ ቀጠሮ ይያዙ እና ስለ ድጋሚ ማረጋገጫው እንዲሁም ስለ ኪራዩ የሚለወጥ ነገር ካለ ይወያዩ። ለትብብርዎ እናመሰግናለን።

ስለትብብርዎ እናመሰግናለን።

ከሰላምታ ጋር

**"የሚፈረመው የኪራይ ውል የእንግሊዝኛው ቅጂ ብቻ ይሆናል።"**

(የአስተዳደር ኤጀንት፣ የነዋሪዎች ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ ወዘተ / Managing Agent, Resident Manager, etc.)